የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 39
ADDIS ABABA, 15th February, 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፪/፳፻፰ ዓ.ም
የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ……………………ገጽ ፰ሺ፰፻

**CONTENTS**

Proclamation No. 922/2015
Authentication and Registration of Documents' Proclamation……………………………Page 8800

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፪/፳፻፰

**የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ**

በአገር እና በአለም አቀፍ ደረጃ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች መስተጋብሮችን በሚመለከት የሚፈፀሙ የውል እና ሌሎች ግንኙነቶችን በሕግ አግባብ በማረጋገጥ እምነት የሚጣልበት ሰነድ በማመንጨት እንዲሁም ሰነዶችን መዝግቦ በመያዝ በማናቸውም ጊዜ እንዲገኙ በማድረግ ለሕገ-መንግስታዊ መብቶች ዋስትና መስጠት በማስፈለጉ፤

የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ተግባር በመላ አገሪቱ ወጥ የሆነ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ፣ አገር አቀፍና አለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አሰራር እንዲኖረው የሚያስችል ሕግ በማስፈለጉ፤

በሰነድ አረጋጋጭና መዝጋቢ ተቋማት መካከል ግልጽ ግንኙነት የሚፈጥር እና ያለአግባብ የሚረጋገጡ ሰነዶችን መቆጣጠር የሚያስችል የተሻሻለ ሥርዓት መኖሩ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማቀላጠፍ እንዲሁም አሰራሩን ተገማች በማድረግ በሀገሪቱ ውስጥ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የበለጠ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ እና እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያሉትን የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሕጎች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## PROCLAMATION No. 922/2015

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AUTHENTICATION AND REGISTRATION OF DOCUMENTS**

WHEREAS, authentication of documents provide reliable means of evidence and thus facilitate social, economic, contractual and other relations between persons both at domestic and international levels as well as registration of documents ensures availability of documents whenever required and provide guarantees for constitutional rights;

WHEREAS, it has become necessary to put in place law and procedure that meets international standard to make the activities of authentication and registration of documents uniform, effective and efficient all over the country;

WHEREAS, it has become necessary to amend the existing laws of authentication and registration of documents to create transparent relations between authentication and registration institutions and supervising improperly certified documents and to enable to have efficient economic and social relations among persons as well as to make the procedures predictable and thereby to create one economic community;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፮) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፪/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ሰነድ" ማለት ማናቸውም ውል፣ ኑዛዜ፣ የውክልና ሥልጣን መስጫና መሻሪያ ሰነድ፣ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ጽሁፎችን ለመተርጎም ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተተረጎመ ጽሁፍ፣ የሰነድ ቅጂ ወይም ግልባጭ፣ የወሳኝ ኩነት ሰነድ፣ የትምህርትና የሙያ ፈቃድ ማስረጃ፣ የማኅበራት መመስረቻ ጽሁፍ እና/ወይም መተዳደሪያ ደንብ፣ ቃለ ጉባዔ ወይም ማናቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገብ የቀረበ ጽሁፍ ነው፤

፪/ "ሰነድ ማረጋገጥ" ማለት አዲስ ሰነድ በአዘጋጁ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ሲፈረም ማየትና ይኸው መፈፀሙን በማረጋገጥ በሰነዱ ላይ መፈረምና ማኅተም ማድረግ ወይም አስቀድሞ በተፈረመ ሰነድ ላይ የሚገኝ ፊርማንና ወይም ማኅተምን በቃለ መሀላ ወይም ማኅተም ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ በሰነዱ ላይ መፈረምና ማኅተም ማድረግ ነው፤

፫/ "ሰነድ መመዝገብ" ማለት አንድን ሰነድ ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ መለያ ቁጥር በመስጠት መመዝገብና ማስቀመጥ ወይም በሕግ መሠረት በሰነድ አረጋጋጭና መዝጋቢ ተቋም ዘንድ እንዲቀመጥ የተባለ ሰነድን ተቀብሎ መመዝገብና ማስቀመጥ ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Authentication and Registration of Documents' Proclamation No. 922/ 2015".

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "document" means any contract, will, document of power of attorney or revocation, a document translated from one language into another by a licensed translator, copy of a document, document of vital event, education and professional certificate, memorandum or/and articles of association, minutes or any written matter submitted for authentication and registration in accordance with this Proclamation;

2/ "to authenticate a document" means to sign and affix a seal by witnessing the signing of a new document by the person who has prepared such document or the person it concern and after ascertaining that this formality is fulfilled; or to sign and affix a seal on an already signed document by ascertaining its authenticity through an affidavit or specimen signature and/or seal;

3/ "to register a document" means to register a document in a register prepared for the purpose by giving identification number or to register and deposit a document which is required by law to be deposited with authentication and registration institution;

፬/ "ተቋም" ማለት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ተግባራትን እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል አካል ነው፤

፭/ "ሰነድ አረጋጋጭ" ማለት ሰነድ ለማረጋገጥ እና ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው ተቋማት ውስጥ ሰነድ የማረጋገጥ ስራ የሚሰራ ሠራተኛ ነው፤

፮/ "ሚኒስቴር" ማለት የፍትሕ ሚኒስቴር ነው፤

፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤

፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ ሰነድ የማረጋገጥ እና የመመዝገብ ሥልጣንና ተግባር በተሰጠው የፌዴራልና የክልል ተቋም እንዲሁም ይህ ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ በተሰጣቸው ሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላት በሚያረጋግጧቸውና በሚመዘግቧቸው ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ሰነድ የሚያረጋግጡና የሚመዘግቡ ተቋማት እና ዓላማዎች</u>

**፬. <u>የፌዴራል ተቋም</u>**

ሰነዶችን የማረጋገጥና የመመዝገብን ተግባር በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያስተባብር እና የሚደግፍ፣ የተረጋገጡና የተመዘገቡ ሰነዶችን መረጃ በመረጃ ቋት በማዕከል አደራጅቶ የሚይዝ እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ተግባራትን የሚያከናውን አግባብ ያለው የፌዴራል ተቋም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይቋቋማል፡፡

**፭. <u>የክልል ተቋም</u>**

፩/ ክልሎች ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽሙ ተቋማትን ያደራጃሉ፡፡

4/ "institution" means a federal or regional organ duly authorized to perform duties of authentication and registration of documents;

5/ "notary" means a person who is employed to authenticate a document in an institution duly authorized by law to authenticate and register documents;

6/ "Ministry" means the Ministry of Justice;

7/ "region" means any state referred to under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

8/ "person" means any natural or judicial person;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall apply to documents to be authenticated and registered by the federal and regional institutions vested with the powers and duties to authenticate and register documents as well as by the other federal government organs vested with such powers and duties in this Proclamation.

## <u>PART TWO</u>
## <u>AUTHENTICATION AND REGISTRATION INSTITUTIONS AND OBJECTIVES</u>

**4. <u>Federal Institution</u>**

An appropriate federal Institution shall be established by regulation of the Council of Ministers to nationally coordinate and support the authentication and registration activities, to organize and keep central data base for documents authenticated and registered and to perform activities of document authentication and registration in Addis Ababa and Dire Dawa cities.

**5. <u>Regional Institution</u>**

1/ Regions shall establish institutions for enforcement of this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በክልሎች የሚቋቋሙት ተቋማት አደረጃጀት እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በክልሉ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫/ የክልል ተቋማት ሀገራዊ ሰነድ የማረጋገጥ እና የመመዝገብ ሥርዓቱን ወጥነት ለማስጠበቅ ሲባል አረጋግጠው ስለሚመዘግቧቸው ሰነዶች አስፈላጊውን መረጃ ለፌዴራሉ ተቋም የመላክ እንዲሁም ሌሎች ትብብሮችን የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**፯. ሰነድ የማረጋገጥ ሥልጣንና ተግባር ስለተሰጣቸው ሌሎች የፌዴራል መንግስት አካላት**

በሌላ ህግ ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተቋማት ሰነድ የማረጋገጥ ስልጣን አላቸው፦

፩/ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሰነዶችን ያረጋግጣሉ፡፡

፪/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፦

ሀ) በኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የተረጋገጡ ሰነዶችን፤

ለ) በተቀባዩ አገር ሕግ እንዲረጋገጡ የሚፈለጉ እና ወደ ውጭ የሚላኩ ሰነዶችን፤

ያረጋግጣል፡፡

፫/ የመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች በግዳጅ ላይ የሚገኙ የሠራዊቱ አባላት የሚያቀርቡላቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

፬/ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ከታራሚዎች ወይም ከቀጠሮ እስረኞች የሚቀርቡላቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

2/ The structure of the institutions to be established in accordance with sub-article (1) of this Article shall be determined by respective regions based on their objective realities.

3/ Regional institutions shall, for the purpose of maintaining the uniformity of national document authentication and registration system, have a responsibility to send to the federal institution the necessary data of documents they authenticated and registered as well as to implement other collaborative activities.

**6. Other Federal Government Organs Vested with the Powers and Duties of Authentication of Document**

Notwithstanding the document authentication and registration powers given to the Organs by other laws, the following organs shall have the power of document authentication.

1/ The Ethiopian Embassies and Consular Offices shall authenticate documents to be sent to Ethiopia.

2/ The Ministry of Foreign Affairs shall authenticate:

a) documents authenticated by Ethiopian Embassies and Consular Offices and by embassies and consular offices of foreign countries in Ethiopia;

b) documents that are to be sent abroad and require authentication under the law of the receiving country.

3/ Commanders of divisions of the defense force shall authenticate documents submitted by members of the defense force who are on active duty.

4/ Heads of federal prisons shall authenticate documents submitted to them by prisoners or detainees.

፭/ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የክፍል ሹሞች በግዳጅ ላይ ከሚገኙ የፌደራል የፖሊስ አባላት የሚያቀርቡላቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

**፯. <u>የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ዓላማዎች</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሚከናወን ማንኛውም የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ተግባር እና ሥርዓት የሚከተሉትን ዓላማዎች መከተል ይኖርበታል፦

፩/ በክልል እና በፌዴራል የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ተቋማት መካከል በትብብር መንፈስ ላይ የተመረኮዘ የአሠራር ግንኙነት መፍጠር፤

፪/ በአንድ አገራዊ ራዕይና ተልዕኮ ዙሪያ የሠነድ ማረጋገጥ እና የመመዝገብ ሥርዓት ወጥነትን ማረጋገጥ፤

፫/ የዜጎችን የግል ንብረት የማፍራት፣ የመጠቀም እና በሕጋዊ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን በማስከበር የፍትሕ ሥርዓቱን በማገዝ የሕግ የበላይነትን ማስጠበቅ፤

፬/ ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሰነዶች ለሕግና ለሞራል የማይቃረኑ መሆናቸውን እንዲሁም ከኢትዮጵያ ወደ ሌሎች ሀገራት የሚላኩ ሰነዶች በሚላኩበት ሀገር እውቅና ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

፭/ የመልካም አስተዳደርን እና የነጻ ገበያ ሥርዓት ግንባታ ጥረቶችን ማሳለጥ፤

፮/ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በመጠቀምና ተቋማዊ አገልግሎት አሠጣጥን የጥራት ደረጃ በማሳደግ ተደራሽነት ያለው አሠራር መፍጠር፤ እና

፯/ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት፡፡

5/ Commanders of divisions of the Federal Police Commission shall authenticate documents submitted by members of the federal police force who are on active duty.

**7. <u>Objectives of Document Authentication and Registration</u>**

Any activity or procedure of documents authentication and registration conducted at federal and regional level in accordance with this Proclamation shall follow the following objectives:

1/ creating cooperative spirit of working relationship among regional and federal institutions conducting document authentication and registration;

2/ ensuring the uniformity of the documents authentication and registration towards to the national vision and mission of the country;

3/ protecting citizens' rights of producing private property, use and transfer through legal means and thereby supporting the justice system and ensuring the rule of law;

4/ ensuring the documents sent from other countries to Ethiopia that they are not against law and moral; and the recognition of documents, in the receiving country, sent to other countries from Ethiopia;

5/ facilitating the efforts of building good governance and free market system;

6/ creating accessible working system by using new technological inputs and by enhancing the quality levels of institutional service;

7/ act in collaboration with stakeholders.

## ክፍል ሦስት
## የሰነድ ማረጋገጥ ተግባራት፣ ሥርዓት እና የአረጋጋጭ ግዴታዎች

### ፰. የሰነድ ማረጋገጥ ተግባራት

የሰነድ ማረጋገጥ ተግባራት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

፩/ ሰነዶችን ማረጋገጥ፤

፪/ የሰነድ ቅጅዎች ከዋናው ጋር አመሳክሮ ማረጋገጥ እና መመዝገብ፤

፫/ ቃለመሀላና በቃለመሀላ የሚሰጥ ማረጋገጫዎችን መቀበል፤

፬/ ባለጉዳዮች ሲጠይቁ እንደአስፈላጊነቱ የፊርማ እና/ወይም የማኅተም ናሙና መያዝ፤

፭/ ለመረጋገጥ የሚቀርቡ ሰነዶችን ሕጋዊነት ማረጋገጥ፤

፮/ ለመረጋገጥ በሚቀርቡ ሰነዶች ላይ የሚፈርሙ ወይም የፈረሙ ሰዎችን ችሎታ፣ መብት እና ሥልጣን ማረጋገጥ፤

፯/ በሕግ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ በሚደረጉ ውሎች፦

ሀ) የንብረት አስተላላፊው ንብረቱን ለማስተላለፍ ያለውን ባለመብትነት፣ እና

ለ) ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያልታገደ መሆኑን፤

ማረጋገጥ፤

፰/ ሰነዶች አግባብ ካለው አካል መመንጨታቸውን ማረጋገጥ፤

፱/ ስለተረጋገጡና ስለተመዘገቡ ሰነዶች ሥልጣን ባለው ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ማስረጃ መስጠት፤

፲/ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን፡፡

### ፱. መረጋገጥና መመዝገብ ያለባቸው ሰነዶች

፩/ የሚከተሉት ሰነዶች በዚህ አዋጅ መሠረት ካልተረጋገጡና ካልተመዘገቡ ሕጋዊ ውጤት አይኖራቸውም፦

ሀ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መረጋገጥና መመዝገብ ያለባቸው ሰነዶች፤

## PART THREE
## AUTHENTICATION ACTIVITIES, PROCEDURES AND DUTIES OF THE NOTARY

### 8. Authentication Activities

The documents authentication activities include the following:

1/ to authenticate documents;

2/ to authenticate and register copies of documents against their originals and register same;

3/ to administer oath and receive affidavits;

4/ to keep custody of specimen of signatures and/or seal upon request by those concerned;

5/ to ascertain the legality of documents submitted for authentication;

6/ to ascertain the capacity, right and authority of persons who are about to sign or who have signed documents submitted for authentication;

7/ to ascertain with respect to contracts made to transfer properties for which title certificates are issued under the law:

a) the right of the transferor to transfer the property; and

b) that the property is not mortgaged or pledged or that such property is not attached by a court order;

8/ to ascertain whether documents are produced by legitimate authority;

9/ to provide evidence upon request by authorized or appropriate organ about authenticated and registered documents;

10/ to conduct other similar activities.

### 9. Documents that shall be Authenticated and Registered

1/ The following documents shall not have legal effect unless they are authenticated and registered in accordance with this Proclamation:

a) documents that shall be authenticated and registered in accordance with the appropriate law;

ለ) የውክልና ሥልጣን መስጫ ወይም መሻሪያ ሰነዶች፤

ሐ) የንግድና ሌሎች ማህበራት መመስረቻ ጽሁፎች፣ መተዳደሪያ ደንቦች እና ማሻሻያዎቻቸው፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከቱት ሰነዶች ውጭ ሌሎች ሰነዶች እንዲረጋገጡና እንዲመዘገቡላቸው ባለጉዳዮች ሲጠይቁ ሰነድ አረጋጋጪ እነዚህን ሰነዶች ያረጋግጣል፤ ይመዘግባል፡፡

**፲. <u>አዲስ ሰነድ ስለማረጋገጥ</u>**

፩/ ሰነድ አረጋጋጪ አዲስ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሲቀርብለት ሰነዱን ለመፈረም የቀረበው ሰው ማንነት፣ ስምና አድራሻው በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ሰው ማንነት፣ ስምና አድራሻ ተመሳሳይ መሆኑን በማስረጃ አመሳክሮ ሰነዱን ያረጋግጣል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰነድ አረጋጋጪ ሰነድ ሲያረጋግጥ አግባብ ባላቸው ሕጎች የተደነገገውን ሥርዓት መከተል አለበት፡፡

**፲፩. <u>አስቀድሞ ስለተፈረሙ ሰነዶች</u>**

፩/ ሰነድ አረጋጋጪ አስቀድሞ የተፈረመ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሲቀርብለት ሰነዱ ላይ የሰፈረው ፊርማ ሰነዱን አስቀድሞ የፈረመው ሰው ፊርማ መሆኑን ወይም በሰነዱ ላይ የሚገኘው ማኅተም ትክክለኛው ማኅተም መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

፪/ የቀረበው ሰነድ በሌላ ሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ ከሆነ በሰነዱ ላይ የሚገኘው ፊርማና ማኅተም የተባለው ሰነድ አረጋጋጭ ፊርማና ማኅተም መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

**፲፪. <u>ስለሰነድ ግልባጭ ወይም ኮፒ</u>**

፩/ የሰነድ ግልባጭ ወይም ኮፒ እንዲረጋገጥ ሲቀርብለት ሰነድ አረጋጋጪ የኮፒው ይዘት ከዋናው ሰነድ ይዘት ጋር እንዲሁም በግልባጩ

b) power of attorney or revocation of power of attorney;

c) memorandum and articles of association of business organizations and other associations, and amendments thereof.

2/ The notary shall authenticate and register documents other than those specified under sub-article (1) of this Article, if requested by the concerned parties.

**10. <u>Authentication of a New document</u>**

1/ Where a new document is submitted for authentication, the notary shall authenticate the document after having ascertained by means of evidence that the name and address of the person who is about to sign the document is the same as the name and address on the document.

2/ Without prejudice to Article 17 of this Proclamation the notary shall comply with the procedures provided for in the relevant laws when authenticating a document.

**11. <u>Documents Already Signed</u>**

1/ Where a document which is already signed is submitted for authentication, the notary shall authenticate such document by ascertaining that the signature on the document is that of the person who has signed it or that the seal on the document is genuine.

2/ Where the document submitted for authentication is already authenticated by another notary, the notary shall authenticate the document by verifying that the signature and seal on the document is the signature and seal of the said notary.

**12. <u>Copies of Documents</u>**

1/ Where a copy of a document is submitted for authentication, the notary shall authenticate the document by ascertaining that the contents of the

ወይም በኮፒው ላይ ያለው ፊርማ እና/ወይም ማኅተም በዋናው ሰነድ ላይ ካለው ፊርማ እና/ወይም ማኅተም ጋር አንድ አይነት መሆኑን በማመሳከር ሰነዱን ያረጋግጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተረጋገጠ ሰነድ የዋናውን ሰነድ ያህል የማስረጃነት ዋጋ ይኖረዋል፡፡

**፲፫. የሰነዶችን ሕጋዊነት ስለማረጋገጥ**

፩/ ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ ከማረጋገጡና ከመመዝገቡ በፊት የሰነዱ ይዘት ሕግን እና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ሰነድ አረጋጋጩ የሰነድን ትክክለኛነት ከማረጋገጥ አልፎ የሰነዱን ይዘት የመለወጥ ወይም የማስለወጥ ሥልጣን የለውም፡፡

**፲፬. የሰነድ ፈራሚዎችን ችሎታና ሥልጣን ስለማረጋገጥ**

፩/ ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ ከማረጋገጡ በፊት የፈራሚውን ወይም ሰነዱን ለመፈረም የቀረበውን ሰው የመፈረም መብት ወይም ሥልጣን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ የሰነድ ፈራሚው ወይም ለመፈረም የቀረበው ሰው የሕግ ችሎታ ያለው መሆኑ አጠራጣሪ ሲሆን ሰነድ አረጋጋጩ የፈራሚውን የሕግ ችሎታ ተገቢ በሆነው መንገድ ማጣራት አለበት፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፭. የንብረቶችን እና የባለንብረቶችን ሁኔታ ስለማረጋገጥ**

አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመረጋገጣቸው በፊት ሰነድ አረጋጋጩ፦

፩/ ንብረት አስተላላፊው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ያለው፤

፪/ ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ፤ እና

copy are the same as that of the original document and that the signature and/or seal on the copy is the same as the signature and/or seal on the original document.

2/ A document authenticated in accordance with sub-article (1) of this Article shall have the same equal value as that of the original document.

**13. Ascertaining the Legality of Documents**

1/ A notary shall, before authenticating and registering a document, ascertain that its contents are not illegal or immoral.

2/ Apart from ascertaining its legitimacy, a notary shall not have power to change or cause to be changed the contents of a document submitted for authentication.

**14. Ascertaining the Capacity and Authority of Signatories of a Document**

1/ The notary shall, before authenticating a document, make sure that the person who has signed or is about to sign the document has the right or authority to sign it.

2/ Where the capacity of a person who has signed or is about to sign a document is doubtful to do so, the notary shall make the necessary investigation in appropriate way.

3/ The Ministry shall issue directive for the application of sub-article (1) of this Article.

**15. Ascertaining the Conditions of Ownership and the Owners of Certain Properties**

Without prejudice to provisions provided by the relevant law, before authenticating documents relating to the transfer of properties for which title certificates are issued under the law, the notary shall ascertain that:

1/ the transferor of the property has title certificate for the property in accordance with the relevant law;

2/ the property is not mortgaged or pledged or is not attached by a court order;

፫/ ሰነዱን የሚፈርመው ወይም ለመፈረም የቀረበው ሰው ሰነዱን ለመፈረም ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ወይም ሥልጣን ያለው፣

መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**፲፮. ቃለ መሀላ ስለመቀበልና የምስክር ቃል ስለመስማት**

፩/ ማንኛውም ሰው የሰነድ ይዘት ትክክለኛነት በሰነድ አረጋጋጪ ፊት ቀርቦ በቃለ መሀላ ማረጋገጥ ይችላል፤ ሰነድ አረጋጋጪም የተባለው ሰው በፊቱ ቀርቦ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃለ መሐላ ማስፈፀሙን በሰነዱ ላይ በጽሑፍ ማስፈር አለበት፡፡

፪/ ሰነድ አረጋጋጭ በፍርድ ቤት ሲታዘዝ የሰውን የምስክርነት ቃል ይቀበላል፡፡

፫/ ሰነድ አረጋጋጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የምስክርነት ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ምስክሩ ቃሉን የሰጠው በገዛ ፈቃዱ መሆኑን የምስክርነት ቃሉ በሰፈረበት ሰነድ ላይ በመጻፍ ይፈርምበታል፤ ማኅተሙንም ያትምበታል፡፡

**፲፯. በጽሁፍ የሚደረጉ ውሎች እና የኑዛዜ ፅሁፎች ላይ ስለሚቀርቡ ምስክሮች**

፩/ ሰነዶችን ለማረጋገጥና ለመመዝገብ ሥልጣን በተሰጠው ተቋም ፊት ቀርበው ከሚረጋገጡና ከሚመዘገቡት ሰነዶች መካከል፦

ሀ) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ባለቤትነት በሽያጭ ወይም በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች፤

ለ) በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የመያዣ ወይም የዋስትና መብት ለማቋቋም የሚደረጉ ውሎች፤ እና

ሐ) በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ፤

በሁለት ምስክሮች መፈረም አለባቸው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች እንዲረጋገጡና እንዲመ ዘገቡ የሚቀርቡ ሰነዶች በምስክሮች መፈረም ሳያስፈልግ ሊረጋገጡና ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

**፲፰. ሰነዶችን ስለመመዝገብና ስለማስቀመጥ**

፩/ ሰነድ አረጋጋጪ የሚያረጋግጣቸውን ሰነዶች ይመዘግባል፤ ለእያንዳንዱ ሰነድ አንድ ግልባጭ በተቋሙ ያስቀምጣል፡፡

3/ the person who has signed or is about to sign the document has legal or contractual right or authority to sign the document.

**16. Administration of Oath and Hearing of Witness**

1/ Any person may declare the truth of the contents of a document under oath before a notary; in such a case, the notary shall write down on the document that he caused the said person to sworn before he made the declaration.

2/ A notary shall take the testimony of a witness where he is ordered by a court.

3/ Where the notary takes the testimony of a witness under sub-article (2) of this Article, he shall write on the document that the witness has given his testimony of his free will; and sign on the document and affix his seal thereon.

**17. Witnesses to be Present for Written Contracts and Documents of will**

1/ From the documents submitted for authentication and registration, the following documents shall be signed before the relevant authentication and registration institution by two witnesses:

a) contracts of transfer of ownership of immovable properties by selling or donation;

b) contracts of establishing collateral or guarantee right on immovable properties; and

c) Public will.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, other documents may be authenticated and registered without being signed by witnesses.

**18. Registration and Deposit of Documents**

1/ The notary shall register all documents which he authenticates and deposit a copy of each document in the institution.

፪/ ሰነድ በተቋም ዘንድ እንዲቀመጥ በሕግ የተደነገገ ከሆነ ሰነድ አረጋጋጩ እንዲህ ያለው ሰነድ ሲቀርብለት ተቀብሎ ይመዘግባል፤ ያስቀምጣል፡፡

፫/ በተቋም ዘንድ እንዲቀመጥ የተደረገ የሰነድ ግልባጭ ወይም ሰነዱ በተቋሙ ዘንድ ስለመኖሩ ማስረጃ እንዲሰጠው ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ሲጠየቅ ሰነድ አረጋጋጩ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ግልባጩን ወይም ማስረጃውን ይሰጣል፡፡

**፲፱. ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ አገልግሎት ስለመስጠት**

፩/ ወደ ሰነድ አረጋጋጩ መደበኛ የሥራ ቦታ ለመሄድ የማይችል ሰው አገልግሎት ሲጠይቅ ሰነድ አረጋጋጩ የቅርብ የሥራ ኃላፊውን ፈቃድ ሲያገኝ በጠያቂው አድራሻ በመገኘት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለተመለከተው አገልግሎት የሚከፈለው ተጨማሪ ክፍያ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፬ (፪) መሠረት ይወሰናል፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፳. ክልከላ**

፩/ ሰነድ አረጋጋጭ፡-

ሀ) የራሱን፣ የባለቤቱን፣ የወላጆቹን ወይም የተወላጆቹን፣ የወንድም ወይም የእህቱን፣ የትዳር አጋር ወላጆችን እንዲሁም የሚስት ወይም የባል ወንድም ወይም እህትን ሰነድ፤

ለ) ራሱ ወኪል ወይም እንደራሴ የሆነለትን ሰው ሰነድ፤ እና

ሐ) ተጠቃሚ የሆነበትን የንግድ ድርጅት ወይም ማኅበር ሰነዶች፤

ማረጋገጥ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ሰነድ አረጋጋጩ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ሲሆን ሰነዱ በሌላ ሰነድ አረጋጋጭ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

2/ Where the law provides for the deposit of a document within institution, the notary shall register and deposit such document upon its submission.

3/ The notary shall, upon request by an interested person to get a copy or evidence about a document deposited in the institution, give the requested copy or evidence upon receipt of appropriate service fee.

**19. Rendering Service Outside the Official Place of Work**

1/ Where a person who is not capable to go to the official place of work of the notary request to get the service, upon approval by the immediate officer above him, the notary shall render service for such person at the latter's address.

2/ For the service rendered pursuant to sub-article (l) of this Article the amount of additional service fee to be charged shall be determined in accordance with Article 34 (2) of this Proclamation.

3/ The Ministry shall issue directive for the application of sub-article (1) of this Article.

**20. Prohibition**

1/ A notary shall not authenticate:

a) his own document, document of his spouse, document of his ascendant or descendant, document of his brother and sister, document of his spouse parents as well as document of brothers or sisters of his spouse;

b) document of a person for whom he acts as an agent or representative; and

c) document of a business organization or association to which he is beneficiary.

2/ If the condition specified under sub-article (1) of this Article happens, the notary shall have the obligation to notify, and the document shall be authenticated by another notary.

፫/ በሕግ እንዲሟሉ የተጠየቁት ሁኔታዎች እስካልተሟሉ ድረስ ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ የማረጋገጥ እና የመመዝገብ አገልግሎት አይሰጥም፡፡

**፳፩. ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ**

፩/ ማንኛውም ሰነድ አረጋጋጭ በፍርድ ቤት ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ካልታዘዘ በቀር በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን መረጃ ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሰነድ አረጋጋጩ ወንጀል ስለመፈጸሙ ጠቋሚ መረጃዎች ሲያገኝ ጉዳዩን አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

**፳፪. ከኢትዮጵያ ስለሚወጡና ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገቡ ሰነዶች**

ከኢትዮጵያ ወደ ሌሎች ሀገራት እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ ሰነዶች የሚረጋገጡበትና የሚመዘገቡበት ተጨማሪ ዝርዝር ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**፳፫. የተረጋገጡና የተመዘገቡ ሰነዶች ሕጋዊ ውጤት**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ እና ፳፯ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት የተረጋገጠ ሰነድ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

፪/ ተረጋግጦ የተመዘገበን ሰነድ በክርክር ሂደት ውስጥ መቃወም የሚቻለው ፍርድ ቤት በበቂ ምክንያት ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡

**፳፬. ተረጋግጦ የተመዘገበ ሰነድ ተቀባይነት**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በፌዴራል ተቋም ወይም አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ ማንኛውም ሰነድ በክልል መንግስታት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

3/ The notary shall not give any authentication and registration service unless the requirements of the law are satisfied.

**21. Obligation to Keep Confidentiality**

1/ A notary shall not give to third party information, which comes into his possession in the course of performing his duties, unless ordered by a court or by a body empowered by law.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the notary shall, when he accesses indicatory information as to the commission of a crime, report the matter to the appropriate government organ.

**22. Document Sent from and into Ethiopia**

Additional detailed procedures for the authentication and registration of documents sent from Ethiopia to other countries and; those sent from other countries to Ethiopia shall be regulated by regulation to be issued by the Council of Ministers.

**23. Legal Effects of Authenticated and Registered Documents**

1/ Without prejudice to Articles 25 and 27 of this Proclamation, a document authenticated and registered in accordance with this Proclamation shall be conclusive evidence of its contents.

2/ Authenticated and registered documents may, during proceeding, be challenged only with the permission of a court for good cause.

**24. Acceptance of Authenticated and Registered Documents**

1/ Any document authenticated and registered by a federal institution or organ in accordance with this Proclamation shall be acceptable by Regional Governments.

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት በክልል ተቋም የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ በተመሳሳይ ሁኔታ በፌዴራል መንግስትና በሌሎች የክልል መንግስታት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አራት
## ያለአግባብ ስለተረጋገጡ እና ስለተመዘገቡ ሰነዶች

**፳፭. ያለአግባብ የተረጋገጡ እና የተመዘገቡ ሰነዶችን አግዶ ስለማቆየት**

፩/ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው አመልካችነት ወይም በተቋሙ በራስ አነሳሽነት ሰነድ ያለአግባብ ተረጋግጦ መመዝገቡ በበቂ ማስረጃ ሲደረስበትና ሰነዱ በአስቸኳይ ካልታገደ በቀር ሊደርስ የሚችለው ጉዳት በቀላሉ ሊመለስ የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ተቋሙ አረጋግጦ በመዘገበው ሰነድ ላይ ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዝ ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡

፪/ ሰነድ ያለአግባብ ተረጋግጦ ተመዝግቧል የሚባለው ሰነዱ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፩) መሰረት ሰነድ እንዳያረጋግጡ በተከለከሉ አረጋጋጮች፣

ለ) መሠረታዊ የሆኑ የማረጋገጥና የምዝገባ መስፈርቶች ወይም ፎርማሊቲዎች ሳይሟሉ በመታለፍ፣ ወይም

ሐ) ሕጋዊ ያልሆኑ ሰነዶች በማቅረብ፣

ባይሆን ኖሮ ሰነዱ ሊረጋገጥና ሊመዘገብ የማይችል የነበረ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

**፳፮. ያለአግባብ ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶችን ለማገድ መከተል ስለሚገባ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ ሰነድን አግዶ የማቆየት ትዕዛዝ የሚሰጠው ሰነዱ ላይ ከሦስት የማያንሱ የተቋሙ ባለሙያዎች ባሉበት ቡድን አስፈላጊው ማጣራት ከተደረገ በኋላ በተቋሙ የበላይ ሀላፊ ይሆናል፡፡

፪/ ሰነድን አግዶ የማቆየት ውሳኔ ሰነዱ እንዲታገድ ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ወይም ሰነዱ የሚታገደው በተቋሙ በራስ ተነሳሽነት ከሆነ ማጣራት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ባሉት አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መሰጠት አለበት፡፡

2/ Any document authenticated and registered by a regional institution in accordance with this Proclamation shall, in a similar manner, be acceptable by the Federal Government and other Regional Governments.

## PART FOUR
## IMPROPERLY AUTHENTICATED AND REGISTERED DOCUMENTS

**25. Suspensions of Improperly Authenticated and Registered Documents**

1/ The institution may, if it is proved by adequate evidence, pass temporary order of suspension on improperly authenticated and registered documents when petition is lodged by concerned person or by its own initiative and it is proved that failure to suspend may cause serious damage that may not be easily reversible.

2/ A document is said to be improperly authenticated and registered only when it could not have been authenticated and registered had it not been:

a) by notaries prohibited pursuant to Article 20 (1) of this Proclamation;

b) performed without completing basic authentication and registration procedures or formalities; or

c) by producing illegal documents.

**26. Procedures to be Followed for Suspension of Improperly Authenticated and Registered Documents**

1/ The order of suspension of a document shall be given by the head of the institution after the necessary examination being conducted by a team of professional not less than three in number drawn from the institution.

2/ The order of suspension of a document shall be given within five working days from the date of submission of the petition or from the date examination commenced if the suspension is initiated by the institution.

**፳፯. <u>ሰነድን አግዶ የማቆየት ውጤት</u>**

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፭ (፩) መሠረት ሰነድ ታግዶ በሚቆይበት ወቅት ሰነዱ ተረጋግጦ እንዳልተመዘገበ ይቆጠራል፡፡

**፳፰. <u>በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ ግዴታ</u>**

፩/ ሰነድን የተመለከተ የእግድ ውሳኔ በተላለፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፦

ሀ) ሰነዱ ላይ ወይም በሰነዱ በተከበረው መብት ላይ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው፤ ወይም

ለ) ሰነዱ የታገደው በተቋሙ በራስ አነሳሽነት ሆኖ ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው ማግኘት ካልቻለ ወይም ከሌለ ሰነዱ ላይ በተቋሙ፤

ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መደበኛ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተቋሙ የሰጠውን የዕግድ ውሳኔ እንደሁኔታው ማጽናት፣ ማሻሻል ወይም መሻር ይችላል፡፡

**፳፱. <u>ሰነድ የማገድ ወይም ያለማገድ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ባለው ወገን የሚቀርብ ክስ</u>**

ተቋሙ በሰጠው ሰነድን የማገድ ትእዛዝ መብቱ የተነካ ሰው ወይም እንዲታገድ ጥያቄ አቅርቦ ተቋሙ በሰጠው ሰነድን ያለማገድ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፴. <u>የሰነድ እገዳ ትዕዛዝ ቀሪ ስለመሆን</u>**

በተቋሙ ሰነድን ስለማገድ የተሰጠ ትእዛዝ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ቀሪ ይሆናል፦

፩/ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የሰነድ እገዳ ውሳኔው አይጸናም ብሎ ሲወሰን፤ ወይም

፪/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፰ (፩) መሠረት ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ወይም ተቋሙ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት ክስ ሳያቀርብ ሲቀር፡፡

**27. <u>Effects of Suspension of Document</u>**

During the time of suspension of a document in accordance with Article 25 (1) of this Proclamation, the document shall be considered as not authenticated and registered.

**28. <u>Duty to Institute Proceeding on Regular Court</u>**

1/ When a document is suspended:

a) the concerned person regarding to the document or the right respected with the document, or

b) the institution, in case where concerned person is unavailable or absent, with regard to the document,

shall institute proceedings in a regular court having jurisdiction within one month from the date of order of suspension.

2/ The court received case in accordance with sub-article (1) of this Article may, as the case may be, approve, amend or repeal the order of suspension.

**29. <u>Action Lodged by the Aggrieved Party Against Order of Suspension or Refusal of Suspension</u>**

Any party whose right is affected by the suspension order or who has grievance on the denial of suspension order by the institution may institute case in a court having jurisdiction.

**30. <u>Discarding Suspension Order</u>**

Order of suspension shall be discarded in one of the following conditions:

1/ if the court having jurisdiction invalidate the order of suspension;

2/ if the concerned person does not institute proceeding in a court within one month in accordance with Article 28 (1) of this Proclamation.

**፴፩. የሰነድ አረጋጋጩና መዝጋቢው ተጠያቂነት**

ሰነድን ያለአግባብ ያረጋገጠ ወይም የመዘገበ ማንኛውም ሰነድ አረጋጋጭ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፴፪. በፍርድ ቤት መደበኛ ክስ ከቀረበ በኋላ የሚቀርቡ አቤቱታዎች**

በዚህ አዋጅ የተደነገገው ያለአግባብ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድን ለጊዜው አግዶ ለማቆየት ለተቋሙ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት መደበኛ ክስ ከቀረበ በኋላ ያለአግባብ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ እንዲታገድ የሚቀርቡ አቤቱታዎች መታየት ያለባቸው በፍርድ ቤቱ ነው፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፫. አቤቱታ የማቅረብ መብት**

፩/ ሰነድ አረጋጋጭ በዚህ አዋጅ መሠረት መስጠት ያለበትን አገልግሎት ቢከለክል ወይም አዋጁን በመተላለፍ አገልግሎት ቢሰጥ ማንኛውም ቅሬታ ያለው ሰው ለሰነድ አረጋጋጩ የበላይ ኃላፊ በ፲፭ የሥራ ቀን ውስጥ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ ባለጉዳዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው ወይም አቤቱታው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካላገኘ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፴፬. ስለቴምብር ቀረጥ እና አገልግሎት ክፍያ**

፩/ ሰነድ አረጋጋጩ ሰነዱን አረጋግጦ ከመመዝገቡ በፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የቴምብር ቀረጥ መከፈሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት የሚሰጠው ተመጣጣኝ የሆነ የወጪ መሸፈኛ የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ይሆናል፡፡

፫/ የአገልግሎት ክፍያው መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**31. Liability of a Notary**

Any notary improperly authenticated or registered a document shall be liable in accordance with relevant law.

**32. Lodging Petition after Formal Proceeding in Court**

Without prejudice to the power of the institution to pass temporary order of suspension on documents improperly authenticated and registered in accordance with the provisions of this Proclamation, any petition seeking order of suspension of improperly authenticated and registered documents after formal proceeding in the court shall be handled by the court.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**33. Right to Lodge Petition**

1/ Any aggrieved person may submit a complaint to the superior officer of the notary within 15 working days where the notary refuses to give service that is required of him in accordance with this Proclamation or gives service in violation of this Proclamation.

2/ Where the party who has submitted a complaint pursuant to sub-article (1) of this Article is not satisfied with the decision rendered or where no decision is rendered within 30 days from the date of submission of the petition, he may bring action in a court having jurisdiction.

**34. Payment of Stump Duty and Service Fee**

1/ The notary shall make sure the payment of stump duty pursuant to the relevant law before authenticating and registering a document.

2/ The authentication and registration service shall be given by charging reasonable service fee as cost recovery.

3/ The amount of service fee shall be determined by regulation to be issued by the Council of Ministers.

**፴፭. የመተባበር ግዴታ**

በሌሎች ሕጎች የተመለከቱት ሰነድን ወይም መረጃን ሚስጢራዊነት የመጠበቅ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰነድ አረጋጋጭ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ሰነድ ወይም መረጃ ሲጠይቅ ማንኛውም ሰው የተጠየቀውን ሰነድ ወይም መረጃ በመስጠት ወይም በማቅረብ መተባበር አለበት፡፡

**፴፮. ቅጣት**

የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የተላለፈ ማንኛውም ሰነድ አረጋጋጭ ወይም ሰው በወንጀል ሕጉ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

**፴፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ክልሎች በዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በወጡ ደንቦች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላሉ፡፡

**፴፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፬ እና በአንቀጽ ፴፯ (፩) መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የፌዴራል ተቋም እስኪቋቋም ድረስ በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭ (በአዋጅ ቁጥር ፬፻፷፯/፲፱፻፺፯ እንደተሻሻለው) ውስጥ የተካተቱት የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም አደረጃጀት የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ይቆያሉ፡፡

**35. Duty to Cooperate**

Without prejudice to the provisions of other laws specifying duty to keep confidentiality of documents and information, any person required by a notary to give a document or information necessary for the activities of a notary shall cooperate by producing the required document or by providing the required information.

**36. Penalty**

Any notary or person who violets the provision of this Proclamation shall be penalized in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code or other relevant law.

**37. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Regional States may issue additional law for issues not covered under this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The Ministry may issue directive for the implementation of the regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

**38. Transitory Provisions**

1/ Until the federal institution is established by regulation to be issued by the Council of Ministers pursuant to Article 4 and Article 37 (1) of this Proclamation, the powers and duties as well as the structure of the notary offices provided for under the Authentication and Registration of Documents Proclamation No. 334/2003 (as amended by Proclamation No 467/2005) shall continue to operate.

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት በክርክር ላይ ያሉ ማናቸውም ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭ (በአዋጅ ቁጥር ፬፻፷፯/፲፱፻፺፯ እንደተሻሻለው) ፍፃሜ ያገኛሉ።

**፴፱. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭ (በአዋጅ ቁጥር ፬፻፷፯/፲፱፻፺፯ እንደተሻሻለው) በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፵. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ Notwithstanding Article 39 (1) of this proclamation, any pending issues before the effective date of this proclamation shall be finalized in accordance with Authentication and Registration of Documents Proclamation No 334/2003 (as amended by Proclamation No 467/2005).

**39. <u>Repeal and Inapplicable Laws</u>**

1/ Without prejudice to Article 38 of this Proclamation, the Authentication and Registration of Documents Proclamation No. 334/2003 (as amended by Proclamation No 467/2005) is hereby repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice inconsistent with the provisions of this Proclamation shall apply to matter covered under this Proclamation.

**40. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of February , 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**